ከዓለም አጅግ የተዋበችውንና
አስደሳች የሆነችውን ምድር
ልሰጥህ ፈለግሁ ፤
'አባት' ብለህ እንድትጠራኝና ከእንግዲህ
ወዲህ ፈጽሞ ከእኔ እንዳትለይ
ፈለግሁ ።
20 አንተ ግን ባልዋን እንደ ከዳች ሚስት
ለእኔ ታማኝ አልሆንህም ፤
ይህን እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁ ።"

21 ልምላሜ በሌለባቸው ኰረብቶች ራስ ላይ
ድምፅ ይሰማል ፤
ይህም ድምፅ ፥ የእስራኤል ሕዝብ
እግዚአብሔር
አምላካቸውን በመርሳት ኃጢአት
ሲሠሩ ኖረው ፥
አሁን በመጸጸት የሚያሰሙት የልመና
ድምፅ ነው ።
22 እናንተ ከእግዚአብሔር ርቃችሁ
የነበራችሁ ሁሉ ተመለሱ ፤
እርሱ ይፈውሳችኋል ፤ ታማኞችም
ያደርጋችኋል ።

እናንተም እንዲህ ብላችኋል ፥ "አዎ! እግዚ
አብሔር አምላካችን ስለሆነ ወደ እርሱ እንመለ
ሳለን ፤ 23 በኰረብቶች ራስ ላይ አረማዊ የሆን
ባዕድ አምልኮ መፈጸማችን ምንም አልጠቀመ
ንም ፤ ለእስራኤል ዕርዳታ የሚገኘው ከአምላካ
ችን ከእግዚአብሔር ብቻ ነው ። 24 ነገር ግን
አሳፋሪ ስሆኑ ጣዖታት መስገዳችን ፥ የበግና የከ
ብት መንጋዎቻችንን ሁሉ ፥ ወንዶችና ሴቶች
ልጆቻችንን ሁሉ ፥ ከጥንት ጀምሮ የቀድሞ አባ
ቶቻችን ደክመው ያፈሩልንን ሀብት ሁሉ እንድ
ናጣ አድርጎናል ። 25 እኛና የቀድሞ አባቶቻችን
በመደጋገም ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔር
አምላካችንዖ አሳዝነናል ፤ ትእዛዙንም አልፈጸ
ምንም ፤ ስለዚህ በሐፍረት ልንወድቅና ውርደ
ትም እንደ ልብስ ሊሸፍነን ይገባል ።"

## ምዕራፍ 4

### የንስሓ ጥሪ

1 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፥ "የእስራ
ኤል ሕዝብ ሆይ! እንግዲህ ከተመለሳችሁ ፥
ወደ እኔ ተመለሱ ፤ እኔ የምጠላቸውን ጣዖታት
አስወግዳችሁ ለእኔ ብቻ ታማኞች ብትሆኑ ፥
2 በእውነትና በቅንነት 'ሕያው እግዚአብሔርን'
ብላችሁ መማላችሁ ተገቢ ይሆናል ፤2* አሕዛ
ብም እባርካቸው ዘንድ ይለምኑኛል ፤ ያመሰግኑ
ኛልም ።"

3 እግዚአብሔር ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም
ሕዝብ እንዲህ ይላል ፥ "እዳሪውን መሬት
እረሱ ፤ ዘራችሁን በሾኽ መካከል አትዝሩ ፤
4 እናንተ የይሁዳ ሕዝብና የኢየሩሳሌም ነዋሪ
ዎች ሆይ! የልባችሁን ከፋት ገርዛችሁ አእምሮ
አችሁን በማንጻት ሁለንተናችሁን ለእግዚአብ
ሔር አስገዙ ፤ ይህን ባታደርጉ ግን በከፋ ሥራ
ችሁ ምክንያት ቍጣዬ እንደ እሳት ይነዳል ፤
ቍጣዬም ከነደደ ማንም ሊገታው አይች
ልም ።"

### ይሁዳን ለመውረር የጠላት ዛቻ

5 በምድሪቱ ሁሉ ላይ መለከት ንፉ ፤
ድምፃችሁንም ከፍ አድርጋችሁ
ጩኹ ፤
የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ፤
ወደተመሸጉ ከተሞች እንዲሸሹ
ንገሩአቸው ።
6 ለጽዮን መንገዱን አመልክቱአት ፤
ሳትዘገዩ የደኅንነት ዋስትና
ወደሚገኝበት ስፍራ ሽሹ ፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር ከሰሜን በኩል
መቅሠፍትና ታላቅ ጥፋት ሊያመጣ
ነው ።
7 አንበሳ ከተሸሸገበት ደን እንደሚወጣ ፥
ሕዝብን ሁሉ የሚያጠፋ ይነሣል ፤
እርሱም ይሁዳን ለማጥፋት ይመጣል ፤
የይሁዳ ከተሞች ይፈራርሳሉ ፤
የሚኖርባቸውም አይገኝም ።
8 የእግዚአብሔር ብርቱ ቍጣ ከይሁዳ
ስላልተለየ ፥
ማቅ ለብሳችሁ ዋይ እያላችሁ
አልቅሱ ።

9 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፥ "በዚያን
ቀን ነገሥታትና መኳንንት ወኔ የተለያቸው ፈሪ
ዎች ይሆናሉ ፤ ካህናት ይንቀጠቀጣሉ ፤ ነቢያ
ትም በመገረም አፋቸውን ይይዛሉ ።"
10 እኔም "ልዑል እግዚአብሔር ሆይ! የኢየ
ሩሳሌምን ሕዝብ ማታለል አይሆንብህምን?
'ሰላም ይሆንላችኋል' ብለሃቸው ነበር ፤ አነሆ
አሁን ሰይፍ በአንገታቸው ላይ ተቃጥቶአል"
አልሁ ።
11 የሚያቃጥል ደረቅ ነፋስ ከበረሓ ተነሥቶ
በአነርሱ ላይ የሚነፍስ መሆኑ ለኢየሩሳሌም
ሕዝብ የሚነገርበት ጊዜ ደርሶአል ፤ ይህም
ነፋስ ገለባውን ብቻ ጠራርጎ የሚወስድ ቀላል
ነፋስ አይደለም ፤ 12 በእግዚአብሔር ትእዛዝ
የሚመጣ ነፋስ ስለሆነ ፥ ከሁሉ የበረታ ነው ፤

2* 4፥2 መማላችሁ ተገቢ ይሆናል ፦ ወይም "ብትምሉ ።"
4፥3 ፦ ሆሴዕ 10፥12 ።

ለወፍ ማስፈራሪያ እንደሚተከሉ
ነገሮች ናቸው ፤
መናገር አይችሉም ፤
መራመድ ስለማይችሉ ሰዎች
ይሸከሙአቸዋል ፤
ጉዳት ማድረስም ሆነ ጥቅም
ማስገኘት ስለማይችሉ ፥
ፈጽሞ አትፍሩአቸው ።”

6 እግዚአብሔር ሆይ! አንተን የሚመስል
ማንም የለም ፤
አንተ ኀያል ነህ ፤
ስምህም ታላቅና አስፈሪ ነው ።
7 የመንግሥታት ሁሉ ንጉሥ ስለሆንህ
አንተን የማይፈራ ማን ነው?
በአሕዛብ ጠቢባንም ሆነ
በንጉሥታቶቻቸው መካከል
አንተን የሚመስል ስለሌለ ክብር
ይገባሃል ።
8 ሁሉም ሞኞችና ሰነፎች ሆነው ነው
እንጂ
ከእንጨት ከተሠሩ ምስሎች ከቶ ምን
ትምህርት ማግኘት ይችላሉ?
9 ምስሎቻቸው ከተርሴስ በመጣ ብርና
ከኡፋዝ በተገኘ ወርቅ ተለብጠዋል ፤
በብልኀተኞችም ሥራ አጊጠዋል ፤
ጥበበኞች ሸማኔዎች በሠሩአቸውም
የወይን ጠጅና ሐምራዊ ልብስ
ተሸፍነዋል ።
10 እግዚአብሔር ሆይ! አንተ ግን እውነተኛ
አምላክ ነህ ፤
አንተ ሕያው አምላክ ፥ ዘላለማዊ
ንጉሥ ነህ ፤
አንተ በምትቈጣበት ጊዜ ዓለም
ይናወጣል ፤
የአሕዛብ መንግሥታትም የአንተን
ቊጣ መቋቋም አይችሉም ።

11 ለሌሎች አማልክት የሚሰግዱትን አሕዛብ
ሁሉ
“ሰማይንና ምድርን ያልፈጠሩ የሐሰት
አማልክቶቻችሁ ሁሉ
ከምድረ ገጽ ይደመሰሳሉ” ብላችሁ
ንገሩአቸው ።

### ለእግዚአብሔር የቀረበ ምስጋና

12 እግዚአብሔር በኀይሉ ምድርን ሠራ ፤
በጥበቡም ዓለምን ፈጠረ ፤
በማስተዋሉም ሰማያትን ዘረጋ ፤
13 በእርሱ ትእዛዝ ከሰማይ በላይ ያሉ
ውሃዎች የመናወጥ ድምፅ
ያሰማሉ ፤
እርሱ ደመናዎችን ከምድር ዳርቻ
ያመጣል ፤
በዝናም ጊዜም መብረቅ እንዲበርቅ
ያደርጋል ፤
ነፋስንም ከቤተ መዛግብቱ ይልካል ።
14 ይህንንም እንኳ ካዩ በኋላ
ሰዎች ሞኞችና ዕውቀት የጐደላቸው
ይሆናሉ ፤
አንጥረኞች ለሠሩአቸው ጣዖታት
ይሰግዳሉ ፤
ሕይወት የሌላቸው ሐሰተኞች ስለሆኑ
በሠሩአቸው ምስሎች ያፍራሉ ።
15 እነዚህ አማልክት ከንቱ ስለሆኑ ተንቀው
ይቀራሉ ፤
እግዚአብሔር እነርሱን ለመቅጣት
በሚገሰጥበትም ጊዜ ይደመሰሳሉ ።
16 የያዕቆብ አምላክ ግን እንደነርሱ
አይደለም ፤
እርሱ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው ።
እስራኤልንም የራሱ ወገን እንዲሆን
መርጦታል ፤
ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ነው ።

### ሊመጣ የተቃረበ ስደት

17 የኢየሩሳሌም ሕዝብ ሆይ! እነሆ በጠላት
ስለተከበባችሁ ንብረታችሁን በፍጥነት ሰብ
ስቡ ፤ 18 እግዚአብሔር ከዚህች ምድር ነቃቅሎ
ሊጥላችሁ ተቃርቦአል ፤ ከእናንተ አንድ ሰው
እንኳ እስከማይቀር ድረስ ይሰባብራችኋል ፤ እግ
ዚአብሔር ይህን ተናግሮአል ።
19 የኢየሩሳሌም ሕዝብ እየጮኹ እንዲህ
ይላሉ ፤
“በብርቱ ስለተጐዳን ወዮልን!
ቊስላችንም የማይፈወስ ነው ፤
እኛ ግን ይህን ሁሉ መከራ መታገሥ
የምንችል መስሎን ነበር ፤
20 ድንኳኖቻችን ፈራረሱ ፤
መወጠሪያ ገመዶችም ተቈራረጡ ፤
ልጆቻችን በሙሉ ተሰድደው ስለሄዱ ፥
ድንኳኖቻችንን መልሶ የሚተክልልንና
መጋረጃዎቻችንን የሚሰቅልልን አንድ
እንኳ አልቀረም ።”

21 እኔም እንዲህ ስል መለስሁ ፥
“መሪዎቻችን ሞኞች ከመሆናቸው
የተነሣ ፥
የእግዚአብሔርን ዕርዳታ አልጠየቁም ፤
ውድቀት የደረሰባቸውና ሕዝባችንም
ተበትኖ የቀረው ስለዚህ ነው ።

10፥7 ፦ ራእ. 15፥4 ።

22 አድምጡ አዲስ ዜና መጥቶአል ፤
የሰሜን መንግሥት የይሁዳን ከተሞች
ወደ ምድረበዳነት ለውጦ የቀበሮዎች
መመስጊያ ለማድረግ
በመሬወጥ ላይ ይገኛል ።”
23 እግዚአብሔር ሆይ! ሰው በራሱ ሕይወት
እንደማያዝበትና
አካሄዱንም በራሱ ሥልጣን
መቈጣጠር እንደማይችል
ሀውቃለሁ ።
24 እግዚአብሔር ሆይ! ስለዚህ እኛን
ሕዝብህን መገሠጹን ገሥጸን ፤
ነገር ግን በቊጣህ ፈጽመን እንዳንጠፋ
አትጨክንብን ።
25 ቊጣህን አንተን በማያውቁና ስምህን
በማይጠሩ ሕዝቦች ላይ አፍስሰው ፤
እነርሱ ሕዝብህን ፈጅተዋል ፤
ሁላችንንም ፈጽመው በመደምሰስ ፣
አገራችንን የፍርስራሽ ክምር
አድርገዋታል ።

## ምዕራፍ 11

### ኤርምያስና የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን

1 እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፣ 2 “በቃል
ኪዳኑ የተነገረውን ሁሉ አድምጥ ፤ ለይሁዳና
ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ፣ 3 ይህን ቃል ኪዳን በማ
ይታዘዝ ሁሉ ላይ እርግማን የማመጣ መሆኔን
ንገራቸው ። 4 ይህ ቃል ኪዳን እንደ ጋለ ምድጃ
ከሆነችባቸው አገር ከግብጽ ባወጣኋቸው ጊዜ
ለቀድሞ አባቶቻችሁ የሰጠሁት ነው ፤ ለእኔ እን
ዲታዘዙና እኔ የምላቸውን ሁሉ እንዲፈጽሙ
ነገርሁአቸው ፤ የሚታዘዙኝም ከሆነ እነርሱ
ሕዝቤ እንደሚሆኑና እኔም አምላካቸው እንደ
ምሆን ገለጥሁላቸው ። 5 ይህም ከሆነ አሁን
ያሉባትን ብልጽግና የሞላባትን ለምለም ምድር
የቀድሞ አባቶቻቸው እንዲወርሱ ባደረግሁ ጊዜ
የሰጠኋቸውን የተስፋ ቃል እፈጽማለሁ ።”
እኔም “አሺ ጌታ ሆይ!” አልሁ ።
6 ከዚያን በኋላም እግዚአብሔር እንዲህ
አለኝ፣ “ወደ ይሁዳ ከተሞችና ወደ ኢየሩሳ
ሌም መንገዶች ሄደህ፣ ቃል ኪዳኔን እንዲያዳ
ምጡና ትእዛዛቱን እንዲፈጽሙ በማሳሰብ
ቃሌን ዐውጅላቸው ፤ 7 የቀድሞ አባቶቻቸውን
ከግብጽ ባወጣኋቸው ጊዜ ለእኔ እንዲታዘዙ
በብርቱ አስጠንቀቅሁአቸው ፤ ሕዝቡንም እስከ
ዚህ ቀን ድረስ እንኳ ከማስጠንቀቅ አልተቈጠብ
ሁም ። 8 ነገር ግን ሊያዳምጡኝም ሆነ ሊታዘ
ዙኝ አልፈለጉም ፤ በዚህ ፈንታ እያንዳንዱ ክም
ንጊዜውም ይልቅ እልኸኛና ክፉ ሆኖአል ፤
ቃል ኪዳኔን እንዲፈጽሙ አዘዝሁአቸው ፤ እነ
ርሱ ግን እምቢ አሉ ፤ ስለዚህ በቃል ኪዳኔ የተ
ጻፈውን መቅሠፍት ሁሉ አመጣሁባቸው ።”

9 ቀጥሎም እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፣
“የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሕዝብ በእኔ ላይ አድ
መዋል ፤ 10 እኔ ያዘዝሁአቸውን ለመፈጸም
እምቢ ይሉ እንደነበሩት እንደ ቀድሞ አባቶቻ
ቸው ኃጢአት ይሠራሉ ፤ ባዕዳን አማልክትን
ያመልካሉ ፤ እስራኤልና ይሁዳ በአንድነት ከቀ
ድሞ አባቶቻቸው ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን
አፍርሰዋል ። 11 ስለዚህም እነሆ እኔ እግዚአብ
ሔር በእነርሱ ላይ ጥፋት ሳመጣባቸው ማቀ
ዴን በመግለጥ አስጠንቅቃቸዋለሁ ፤ ያም ጥፋት
በሚመጣበት ጊዜ ማምለጥ አይችሉም ፤ የእኔ
ንም ዕርዳታ ለማግኘት በሚጮኹበት ጊዜ አል
ሰማቸውም ። 12 በዚያን ጊዜ የይሁዳና የኢየሩሳ
ሌም ሕዝብ መሥዋዕት ወደሚያቀርቡላቸው
ባዕዳን አማልክት ሄደው ዕርዳታ እንዲያደርጉላ
ቸው ይጮኻሉ ፤ ነገር ግን እነርሱ ይህ ጥፋት
በሚመጣበት ጊዜ ሊያድኑአቸው አይችሉም ።
13 የይሁዳ ሕዝብ በከተሞቻቸው ልክ ብዙ አማ
ልክት አሉአቸው ፤ የኢየሩሳሌምም ነዋሪዎች
በከተማይቱ በሚገኙ መንገዶች ልክ አስጸያፊ
ለሆነው ባዓል ተብሎ ለሚጠራው ባዕድ አም
ላክ መሥዋዕት የሚያቀርቡባቸው ብዙ መሠዊ
ያዎች ሠርተዋል ። 14 ኤርምያስ ሆይ! ለዚህ
ሕዝብ አማላጅ በመሆን ወደ እኔ አትጸልይ!
እነርሱ ተቸግረው የእኔን ዕርዳታ ለማግኘት
ወደ እኔ በሚጮኹበት ጊዜ አልሰማቸውም ።”
15 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፣ “ሕዝቡ
እኔ አየወደድኋቸው እነርሱ ክፉ ነገር ያደር
ጋሉ ፤ ታዲያ በቤተ መቅደሴ መገኘት ይገባቸዋ
ልን? ከንቱ የሆነ የተስፋ ቃል በመስጠትና የእ
ንስሳት መሥዋዕት በማቅረብስ ጥፋት እንዳይመ
ጣባቸው ለማድረግ የሚችሉ ይመስላቸዋልን?
በዚህስ እንዴት መደሰት ይችላሉ? 16 ‘ቅጠልና
መልካም ፍሬ የሞላበት የወይራ ዛፍ ትመስላ
ችሁ’ ብዬ ነበር ፤ አሁን እንደ ነጐድጓድ የሚ
ያስተጋባ ድምፅ በማሰማት ቅጠሉን በእሳት
አቃጥላለሁ ፤ ቅርንጫፎችንም እሰባብራለሁ ።
17 “እስራኤልንና ይሁዳን የተከልሁ እኔ የሠ
ራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነኝ ፤ ይሁን እንጂ
ባዓል ለተባለው ባዕድ አምላክ መሥዋዕት በማ
ቅረብ እኔን ስላስቈጣችሁ ጥፋት አመጣባችኋ
ለሁ ።”

### በኤርምያስ ላይ የተጠነሰሰ ሤራ

18 ጠላቶቼ በእኔ ላይ ሤራ እንደሚያውጠነ
ጥኑ እግዚአብሔር ገልጦልኛል ፤ 19 በእኔ ላይ
ክፉ ነገር ለማድረግ ማቀዳቸውን ካለማወቄ የተ
ነሣ ፣ ሊታረድ እንደሚነዳ በግ ሆኜ ነበር ፤ እነ
ርሱማ “ይህን ዛፍ ያለ ዕድሜው ቈርጠን
ባጭር እናስቀረው ፤ ዳግመኛ የሚያስታውሰ
ውም እንዳይኖር ድራሹን እናጥፋው” ብለው
ነበር ።

ወደ ፊት ሕዝቡ ይህን ሁሉ በግልጥ ይረዱ
ታል።”
21 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ “በራሳ
ቸው ፈቃድ ሄዱ እንጂ እኔ እነዚህን ነቢያት
አልላክሁአቸውም፤ እኔ ምንም የትንቢት ቃል
አልሰጠኋቸውም፤ እነርሱ ግን በስሜ ትንቢት
ይናገራሉ፤ 22 ምስጢራዊ የሆነውን አሳቤን
ዐውቀው ቢሆንማ ኖሮ ቃሌን ለሕዝቡ ባወጁ
ነበር፤ ጠማማ መንገዳቸውንና ክፉ አኗኗራቸው
ንም እንዲተው ማድረግ በቻሉ ነበር።
23 “እኔ በሁሉ ስፍራ የምገኝ የቅርብ አም
ላክ ነኝ፤ 24 ከእኔ ፊት ተሰውሮ ማምለጥ የሚ
ችል ማንም የለም፤ እኔ በሰማይም በምድርም
በሁሉ ስፍራ እንደምገኝ አታውቁምን?
25 በስሜ ሐሰት የሚናገሩትና ‘ቃሉን በሕልማ
ችን ሰጥቶናል’ የሚሉት ነቢያት የተናገሩትን
ዐውቃለሁ። 26 እነዚያ ነቢያት ራሳቸው በፈጠ
ሩት የሐሰት ቃል ሕዝቤን የሚያስቱት እስከ
መቼ ነው? 27 አባቶቻቸው እኔን እንደረሱና
ዘወር ብለው ባዓልን እንዳመለኩ፥ እነርሱ በሚ
ናገሩአቸው ሕልሞች ሕዝቤ እኔን የሚረሱ
ይመስሉአቸዋል። 28 ሕልም ያለመ ነቢይ
ቢኖር ሕልሙን ብቻ ይናገር፤ ቃሌን የሰማ
ነቢይ ግን ያንኑ ቃል በታማኝነት ይናገር፤
ገለባ ከስንዴ ጋር ምን ግንኙነት አለው?
29 ቃሌ እንደ እሳት፥ አለቱንም ሰባብሮ እንደ
ሚያደቅቅ መዶሻ ነው። 30 አንዱ ከሌላው
ቃልን በመስረቅ ‘ይህ የእግዚአብሔር ቃል
ነው’ እያሉ የሚናገሩትን ነቢያት እጠላለሁ።
31 እንዲሁም ከራሳቸው አመንጭተው እየተና
ገሩ ‘ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው’ የሚሉትን
ነቢያት እቃወማለሁ። 32 እነሆ እኔ እግዚአብ
ሔር የምለውን አድምጡ፤ በሐሰት የተሞላ
ሕልማቸውን የሚናገሩ ነቢያትን እጠላለሁ፤
ይህን ሕልም እየተናገሩ ሐሰት በተሞላ ትምክ
ሕታቸው ሕዝቤን ከእውነተኛ መንገድ ያወ
ጣሉ፤ እኔ አልላክሁአቸውም፤ ወይም ሂዱልኝ
አላልሁአቸውም፤ ለሕዝቡም የሚሰጡት
ጥቅም የለም፤ እኔ እግዚአብሔር ይህን ተናግሬ
አለሁ።”

### ሸክም የሆነ ሕዝብ

33 እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፥ “ኤርምያስ
ሆይ! ነቢይ ወይም ካህን ወይም ከሕዝቤ
አንዱ፥ ‘የእግዚአብሔር ሸክም ምንድን ነው?’
ብሎ ቢጠይቅህ፥ ‘የእግዚአብሔር ሸክም እና
ንተ ናችሁ፤ ስለሆነም ከፊቱ ያስወግዳችኋል’
ብለህ ንገራቸው። 34 ነቢይ ወይም ካህን ወይም
ከሕዝቡ አንዱ ‘የእግዚአብሔር ሸክም’ ብሎ
ከተናገረ እርሱንም ቤተሰቡንም እቀጣለሁ።
35 በዚህ ፈንታ እያንዳንዱ ‘እግዚአብሔር የሰ
ጠው መልስ ምንድን ነው? እግዚአብሔር የተ
ናገረውስ ምንድን ነው?’ በማለት ወዳጆቹንና
ዘመዶቹን መጠየቅ አለበት። 36 ስለዚህ ከእንግ
ዲህ ወዲያ ማንም ሰው ‘የእግዚአብሔር ሸክም’
የሚል ቃል መናገር የለበትም፤ ይህን ቃል
የሚናገር ቢኖር ግን ቃሌ በእርሱ ላይ እውነ
ተኛ ሸክም እንዲሆንበት አደርጋለሁ፤ ሕዝቡ
የሠራዊት ጌታ የሆነውን የሕያው አምላካቸውን
ቃል አጣምመዋል። 37 አንተም ኤርምያስ
ሆይ! ነቢያቱን ‘እግዚአብሔር ምን መልስ ሰጣ
ችሁ? ምንስ ተናገራችሁ?’ ብለህ ጠይቃቸው።
38 ትእዛዜን አፍርሰው ‘የእግዚአብሔር ሸክም’
የሚለውን ቃል የሚናገሩ ከሆነ ግን፥ 39 እነርሱ
ንና ለቀድሞ አባቶቻቸው የሰጠኋቸውን የእነር
ሱን ከተማ ከፊቱ እንደማስወግድ ንገራቸው፤
40 ከቶ የማይረሳና ዘላለማዊ የሆነ ሐፍረትና
ውርደት አመጣባችዋለሁ።”

## ምዕራፍ 24

### ስለ ሁለቱ የበለስ ፍሬ ቅርጫቶች የተነገረ ቃል

1 እግዚአብሔር በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት
የተቀመጡ ሁለት የበለስ ፍሬ ቅርጫቶችን አሳ
የኝ፤ ይህም የሆነው የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነ
ፆር የኢዮአቄም ልጅ የሆነውን የይሁዳ ንጉሥ
ዮአኪንን ከይሁዳ መሪዎች፥ ከእጅ ጥበብ ባለ
ሞያዎችና ከሌሎችም ብልኀተኞች ሠራተኞች
ጋር ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን አስሮ ከወሰደ
በኋላ ነው። 2 የመጀመሪያው ቅርጫት ከሌሎቹ
በፊት ቀደም ብለው የበሰሉ መልካም የበለስ
ፍሬዎችን የያዘ ነው፤ ሁለተኛው ቅርጫት
ደግሞ ለመብል የማይሆኑ የተበላሹ በለሶችን
የያዘ ነው፤ 3 እግዚአብሔርም “ኤርምያስ
ሆይ! ይህ የምታየው ምንድን ነው?” አለኝ።
እኔም “እነሆ የበለስ ፍሬዎችን አያለሁ፤
ጥሩዎቹ ፍሬዎች እጅግ የተዋቡ ናቸው፤ መጥ
ፎዎቹ ፍሬዎች ደግሞ ለምግብነት ደስ የማይ
ሉና እጅግ የተበላሹ ናቸው” ስል መለስሁ
ለት።
4 ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፥
5 “እኔ የእስራኤል አምላክ የሆንሁ እግዚአብ
ሔር ወደ ባቢሎን የተወሰዱት ሕዝብ እንደነ
ዚህ ጥሩ የበለስ ፍሬዎች እንደሆኑ እቈጥራ
ለሁ፤ በደግነትም እከባከባቸዋለሁ፤ 6 ለሕይወ
ታቸውም በመጠንቀቅ ወደዚህች ምድር እንዲ
መለሱ አደርጋለሁ፤ እንጸቸዋለሁ፥ አላፈርሳቸ
ውም፤ እተክላቸዋለሁ፥ አልነቅላቸውም፤
7 እኔ እግዚአብሔር መሆኔን እንዲያውቁ አደር
ጋቸዋለሁ። ከዚያን በኋላም በሙሉ ልባቸው
ወደ እኔ ስለሚመለሱ፥ እነርሱ ሕዝቤ ይሆ
ናሉ፤ እኔም አምላካቸው እሆናለሁ።

24፥1 ። 2ነገ. 24፥12-16፤ 2ዜ.መ. 36፥10።

እኔ እግዚአብሔር ይህን
ተናግሬአለሁ ።”

23 እነሆ የእግዚአብሔር ቍጣ በክፉዎች
አናት ላይ እንደ ዐውሎ ነፋስ ይገለባበጣል ፤
24 ሊያደርገው ያቀደውንም ነገር ሳይፈጽም
አይገታም ፤ በሚመጡትም ቀናት ሕዝቡ ራሳ
ቸው ይህን ሁሉ በግልጥ ይረዱታል ።

## ምዕራፍ 31

### የእስራኤል ወደ አገራቸው መመለስ

1 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፥ “እኔ የእስ
ራኤል ነገዶች ሁሉ አምላክ የምሆንበትና እነር
ሱም ሕዝቤ የሚሆኑበት ጊዜ ይመጣል ፤
2 ከሞት አምልጠው በበረሓ ለሚኖሩ ሕዝብ
በፊቴ ሞገስን እንዲያገኙ አደረግሁ ፤ የእስራ
ኤል ሕዝብ ዕረፍት ለማግኘት በተመኙ ጊዜ ፥
3 እኔ ለእነርሱ ከሩቅ ተገለጥሁላቸው ፤ የእስራ
ኤል ሕዝብ ሆይ! እነሆ እናንተን ሁልጊዜ እወ
ድዳችኋለሁ ፤ ዘላለማዊ ፍቅሬን ለእናንተ ከማሳ
የት አልገታም ፤ 4 እንደገና መልሼ እንጻችኋ
ለሁ ፤ እንደገናም ከበሮአችሁን አንሥታችሁ
በደስታ ትዘፍናላችሁ ፤ 5 እንደገናም በሰማርያ
ኰረብቶች ላይ ወይን ትተክላላችሁ ፍሬውንም
የደከሙበት ሰዎች ይበሉታል ፤ 6 በዚያን ጊዜ
ጠባቂዎች በኤፍሬም ተራራ ላይ ሆነው ‘ኑ
አምላካችን እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ ጽዮን
እንሂድ’ ይላሉ ።”

7 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፥
“ከሕዝቦች ሁሉ ስለምትበልጥ ስለ
እስራኤል በደስታ ዘምሩ ፤
‘እግዚአብሔር ሕዝቡን አድኖአል ፤
በእስራኤል ምድር የቀሩትን ሁሉ
ተቤዥቶአል’
እያላችሁ የምስጋና መዝሙር
አቅርቡ ።
8 እኔ ከሰሜን አመጣቸዋለሁ ፤
ከምድር ዳርቻም እሰበስባቸዋለሁ ፤
ዕውሮች ፥ አንካሶች ፥ ነፍሰጡሮችና
በምጥ የተያዙ ሴቶች ሁሉ ፥
ከእነርሱ ጋር አብረው ይመጣሉ ፤
ታላቅ ሕዝብ ሆነው ወደ አገራቸው
ይመለሳሉ ፤
9 እኔ ወደ አገራቸው ስመራቸው
ሕዝቤ ከደስታ የተነሣ እያለቀሱና
እየጸለዩ ይመለሳሉ ።
በማይሰናከሉበት ለስላሳ መንገድ
ወደ ጥሩ ውሃ ምንጭ እመራቸዋለሁ ።
እኔ ለእስራኤል አባት ነኝ ፤
ኤፍሬምም የበኵር ልጄ ነው ።”
10 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፥
“አሕዛብ ሆይ! አድምጡኝ ፤
በሩቅ ጠረፎችም ቃሌን ሀውጁ ፤
እኔ ሕዝቤን በትኜ ነበር ፤
አሁን ግን እሰበስባቸዋለሁ ፤
እረኛ መንጋውን እንደሚጠብቅም
እጠብቃቸዋለሁ ።
11 እኔ የእስራኤልን ሕዝብ ነፃ
አውጥቻቸዋለሁ ፤
ከኀያል መንግሥትም እጅ በመታደግ
አድኛቸዋለሁ ፤
12 ስለዚህም ተመልሰው መጥተው በጽዮን
ተራራ ላይ በደስታ ይዘምራሉ ፤
በምሰጣቸውም የእህል ፥ የወይን
ጠጅ ፥ የወይራ ዘይት ፥
የበግና የቀንድ ከብት በረከት ሁሉ
ተድላ ደስታ ያደርጋሉ ፤
በቂ ውሃ እንዳገኘች የተክል ቦታ
ይሆናሉ ፤
የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በማግኘት
ከችግርና ከሥቃይ ይድናሉ ።
13 ልጃገረዶቻቸውም በደስታ ይዘፍናሉ ፤
ወንዶች ወጣቶችና ሽማግሌዎችም ደስ
ይላቸዋል ፤
አጽናናቸዋለሁ ፤ ለቅሶአቸውን ወደ
ደስታ ፥
ሐዘናቸውንም ወደ ሐሴት
እለውጣለሁ ፤
14 ካህናቱን በረከት ባለው ምግብ
አጠግባለሁ ፤
የሕዝቡንም ፍላጎት በቸርነቱ
አረካለሁ ፤
እኔ እግዚአብሔር ይህን ተናግሬአለሁ ።”

### የእግዚአብሔር ምሕረት በእስራኤል ላይ

15 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፥
“የለቅሶና የብዙ ዋይታ ድምፅ በራማ
ተሰማ ፤
ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች ፤
ልጆችዋ ስለ ሞቱባት መጽናናት
እምቢ አለች ።
16 ለቅሶአችሁን አቁማችሁ እንባችሁን
ጥረጉ ፤
ስለ ልጆቻችሁ ያደረጋችሁት ነገር
ሁሉ ያለ ዋጋ የሚቀር አይደለም ፤
እነርሱ ከጠላት አገር ተመልሰው
ይወጣሉ ።
17 ልጆቻችሁ ወደ አገራቸው ተመልሰው
ስለሚመጡ ፥
የወደፊት ተስፋ አላችሁ ፤
እኔ እግዚአብሔር ይህን
ተናግሬአለሁ ።

31፥15 ፡- ዘፍ. 35፥16-19 ፥ ማቴ. 2፥18 ።

